# ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
## የእምነት አቋም

1. የብሉያትና የሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ቃል በቃል የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ናቸው። እናት ቋንቋውም/በኩረ ጽሑፉም ሕጸጽ አልባ እንዲሁም በእምነትና በሕይወት ላይ የመጨረሻና የበላይ ባለሥልጣን እንደ ሆነ እናምናለን (1ቆሮንቶስ 2÷7-14፤ 2 ጴጥሮስ 1÷20-21)።

2. የሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆነ አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ እርሱም:— መንፈስ፣ ብርሃን፣ ፍቅር፣ እውነት፣ ዘላለማዊ፣ ሁሉን ቻይ፣ ሕጸጽ አልባ፣ የማይለወጥ፣ ሁሉን ዐዋቂ፣ ጻድቅ፣ ቅዱስ እንደ ሆነ እንዲሁም ይህ እግዚአብሔር ከዘላለም ጀምሮ በሦስት አካልነት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እናምናለን (ዘዳግም 6÷4፤ ኢሳይያስ 45÷5-7 ፤ 1ቆሮንቶስ 8÷4፤ ማቴዎስ 28÷19፤ 2ቆሮንቶስ 13÷14)።

3. እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምን/ሁለንታን እንዲሁም የሕይወትን መሠረታዊ ነገሮች አንደ ኦሪት ዘፍጥረት የፍጥረታት ዘገባ በልዩ ሁኔታ በስድስት ታሪካዊ ቀን እንደ ፈጠረ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የጥንታዊውን ዘመን አስመልክቶ የሚያቀርበው ዘገባ ትክክል እንደ ሆነ ይኸውም አዳምና ሔዋን ልዩ በሆነ ሁኔታ መፈጠራቸውንና የሰው ልጆች ሁሉ አባትና እናት መሆናቸውን፣ ውድቀትና የውድቀቱ ውጤት የሆነው በፍጥረታት ሁሉ ላይ የመጣው መለኮታዊ ርግማን፣ በዓለም ሁሉ የተከሠተው የጥፋት ውሃ፣ የነገዶች ወይም የሕዝቦች መመሥረት እንዲሁም ቋንቋን አስመልክቶ በባቢሎን ግንብ ጊዜ የተከሠተውን ጭምር ሁሉ እናምናለን (ዘፍጥረት 1÷1-31፤ መዝሙር 103÷19፤ ኤፌሶን 3÷9፤ 1ዜና 29÷11፤ ሮሜ 11÷36)።

4. ኢየሱስ ክርስቶስ እምቅድመ ዓለም ጀምሮ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ እንዲሁም ከአብ የተለየ ማንነት ያለውና በሁሉ ነገር ከአብ ጋር እኩል የሆነ አምላክ እንደ ሆነ፣ እኛን ለማዳን ትሥጉት/ሥጋ ሆኖ ከአብ ዘንድ እንደ መጣ፣ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነው ሁሉ ፍጹምም ሰው እንደ ሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ

እንደ ተፀነሰ፣ ከድንግል ማርያም እንደ ተወለደ እናምናለን (ኢሳይያስ 7÷14፣ ማቴዎስ 1÷23:25፣ ሉቃስ 1÷26-35፣ ዮሐንስ 1÷1-3:14፣ 10÷30፣ 14÷9፣ ቈላስይስ 1÷15-17፣ 2÷9፣ ዕብራውያን 1÷2፣ ፊልጵስዩስ 2÷5-8)።

5. ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መጽሐፍ እንደሚል ስለ ኀጢአታችን እኛን የሚተካና እኛን የሚወክል የመሥዋዕት ሞት እንደ ሞተ፣ በእርሱም የሚያምን ሁሉ ከደሙ የተነሣ መጽደቁን እናምናለን (ዮሐንስ 10÷15፣ ሮሜ 3÷24-25፣ 5÷8፣ 1ጴጥሮስ 2÷24፣ ሮሜ 3÷25፣ 5÷8-9፣ 2ቆሮንቶስ 5÷14-15፣ 1ጴጥሮስ 2÷24፣ 3÷18)።

6. መጽሐፍ እንደሚል፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበትና በሞተበት አካል በከበረ ሁኔታ ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ ትንሣኤ የሚያገኙ አማኞች ሁሉ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ የአካል ትንሣኤ እንደሚያገኙ እናምናለን (ዮሐንስ 5÷26-29፣ 14÷19፣ ሮሜ 1÷4፣ 4÷25፣ 6÷5-10፣ 1ቆሮንቶስ 15÷20:23)።

7. ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ እንደ ዐረገ፣ በአባቱ ቀኝ እንደ ተቀመጠ፣ ያከናወነውን ወጀአዊ ሥራ እንዳረጋገጠልን እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሁሉ ራስ እንደ ሆነ፣ ለዳኑት እንደሚቃትት ጠበቃቸውም እንደ ሆነ እናምናለን (ማቴዎስ 28÷6፣ ሉቃስ 24÷38-39፣ ሐዋርያት ሥራ 2÷30-31፣ ሮሜ 4÷25፣ 8÷34፣ ዕብራውያን 7÷25፣ 9÷24፣ 1ዮሐንስ 2÷1)።

8. የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከሺው ዓመት በፊት በቅርቡ እንደሚሆን፣ ምጽአቱም የአማኞች የተባረከ ተስፋ እንደ ሆነ፣ ይህም ታማኝነትን በተሞላ አገልግሎትና ቅዱስና ነቀፋ ለሌለበት ኑሮ እጅግ መሠረታዊ እውነታ እንደ ሆነ እናምናለን (ሐዋርያት ሥራ 1÷9-11፣ 1 ተሰሎንቄ 4÷13-18፣ ራእይ 20)።

9. እግዚአብሔር መጀመሪያ ሰውን በመልኩና በምሳሌው መፍጠሩን፣ ነገር ግን በኋላ በኀጢአት መውደቁን፣

ኀጢአቱም ባስከተለው ውጤት ምክንያት መንፈሳዊ ሕይወቱን እንዳጣ፣ በመንፈሳዊ ነገር ሙት እንደ ሆነ፣ ከዚህም የተነሣ ለዲያቢሎስ ኀይል እንደ ተገዛ፣ ይህ መንፈሳዊ ሙትነትና ሙሉ ለሙሉ በኀጢአት መበላሸት ለሰው ዘር ሁሉ እንደ ደረሰ፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ኀጢአት እንደ ሌለበት፣ ወደዚህች ዓለም የሚመጡ የአዳም ዝርያዎች ሁሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ጭላንጭል እንኳ እንደሌላቸው፣ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ በአካል፣ በአእምሮና በነፍስ እንደ ተመላሹ እናምናለን (*ዘፍጥረት* 2÷7:15-25፤ 3÷1-19፤ *መዝሙር* 14÷1-3፤ *ኢሳይያስ* 43÷7፤ *ኤርምያስ* 17÷9፤ *ያዕቆብ* 3÷9፤ *ቈላስይስ* 1÷16፤ *ዮሐንስ* 3÷36፤ *ሮሜ* 3÷23፤ 6÷23፤ 3÷9-18:23፤ 5÷10-12፤ *ራእይ* 4÷11፤ 1*ቆሮንቶስ* 2÷14፤ *ኤፌሶን* 2÷1-3፤ 1*ጢሞቴዎስ* 2÷13-14፤ 1*ዮሐንስ* 1÷8)።

10. ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታውና አዳኙ እንደ ሆነ የሚያምን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም እንደሚወለድ፣ የእግዚአሔርም ልጅ እንደሚሆን እናምናለን (*ዮሐንስ* 1÷12፤ *ኤፌሶን* 1÷7፤ 2÷8-10፤ 1*ጴጥሮስ* 1÷18-19)።

11. መንፈስ ቅዱስ በግጻዌ መለኮት (Godhead) ውስጥ ሦስተኛው አካል እንዲሁም ከአብና ከወልድ እኩል ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ፣ ስለ ኀጢአት እንደሚወቅስ፣ ዳግም ልደት እንደሚሰጥ፣ በአማኙ እንደሚኖር፣ አማኙን እንደሚያጠምቅ፣ አማኙን እንደሚያትም፣ አማኙን ለቅድስና ሕይወት እንደሚለይ፣ ለክርስቲያኖች በየቀኑ ኀይል እንደሚሰጥ፣ የእግዚአሔርን ቃል እንደሚያስተምር፣ በየቀን ውሎ እንደሚመራ እናምናለን (1*ቆሮንቶስ* 2÷10-13፤ *ኤፌሶን* 4÷30፤ *ዕብራውያን* 9÷14፤ *መዝሙር* 139÷7-10፤ *ኢሳይያስ* 40÷13-14፤ *ሮሜ* 15÷13፤ *ዮሐንስ* 16÷13፤ *ማቴዎስ* 28÷19፤ *ሐዋርያት ሥራ* 5÷3-4፤ 28÷25-26፤ 1*ቆሮንቶስ* 12÷4-6፤ 2*ቆሮንቶስ* 13÷14፤ *ኤርምያስ* 31÷31-34፤ *ዕብራውያን* 10÷15-17)።

12. በአማኞች የዘላለም ዋስትናና የዘላለም ሕይወት እንዲሁም በኃጥአን የዘላለም ቅጣት እናምናለን (*ዮሐንስ* 5÷24፤ 6÷37-40፤ 10÷27-30፤ *ሮሜ* 5÷9-10፤ 8÷1:31-39፤ 1*ቆሮንቶስ* 1÷4-8፤ *ኤፌሶን* 4÷30፤ *ዕብራውያን* 7÷25፤ 13÷5፤ 1*ጴጥሮስ* 1÷5፤ *ይሁዳ* 24፤ *ማቴዎስ* 25÷41፤ *ራእይ* 20÷4-6:11-15፤ *ኤርምያስ* 30÷7፤ *ዳንኤል* 9÷27፤ 12÷1-3፤ 2*ተሰሎንቄ* 2÷7-12)።

13. ኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀትንና የጌታን ራት እንዳካሄደ፣ እስከ ዳግም ምጽአቱም ድረስ ይህንኑ ማድረግ ወይም ማክበር አስፈላጊ እንደ ሆነ፣ አማኞች በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በጥልቅ ውሃ በመስመጥ መጠመቅ እንዳለባቸው፣ የጥምቀት ትርጉሙም ከክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ጋር መተባበራችንን የምናሳይበት ሥርዐት እንደ ሆነ፣ የጌታ ራት የክርስቶስ ቤዛዊ ሞት መታሰቢያ ሥርዐት እንደ ሆነ እናምናለን (1ቆሮንቶስ 11÷28-32፣ 10÷16፣ ማቴዎስ 28÷19፣ ሮሜ 6÷1-11፣ ሐዋርያት ሥራ 2÷38-42፣ 8÷36-39፣)።

14. ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዋጃት፣ አማኞች በደሙ እንደነጹ፣ ዳግም ልደት እንዳገኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንደታተሙ፣ ከዚህ የተነሣ እንደዳኑ ሊያመልኩትና ሊያገለግሉት እንደሚችሉ፣ "እስከ ምድር ዳር ድርስ" ሌሎችን የመፈለግና ለክርስቶስ የመማረክ ዕድልና (privilege) ኀላፊነት እንደ ተሰጣቸው፣ ቅድስና የተሞላው ሕይወት መኖር እንደሚገባቸው፣ መልካሙን ስማቸውን ከሚያጎድፉ ነገሮች መሸሽ እንደሚጠበቅባቸው፣ ጥቅም የሚያገኙበት ቢሆን እንኳ ጥቅማቸውን በመተው እግዚአብሔርን ከማያስከብር ነገር ሁሉ መራቅ እንዳለባቸው እናምናለን (ሮሜ 8:33፣ ሉቃስ 13:3፣ ሐዋርያት ሥራ 2:38፣ ፣ 3:19፣ 11:18፣ ሮሜ 2:4፣ 3:20፣ 8:29፣ 8:9፣ 4:6፣ 10:9-10፣ 1ቆሮንቶስ 12:3፣ 12:13፣ 2ቆሮንቶስ 7:10፣ 4:5፣ 3÷6:18፣ ፊልጵስዩስ 2:11፣ ቈላስይስ 2:14፣ ኢሳይያስ፣ 55:6-7፣ ዮሐንስ 16:7-9፣ ሐዋርያት ሥራ 1:5፣ 2:4፣ ኤፌሶን 2:22፣ 1:13)።

15. ዲያብሎስ አካላዊ ህልውና እንዳለው፣ ታላቅ የሆነ የማታለል ኀይል እንዳለው፣ "በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ" እንደ ሆነ፣ "የዚህ ዓለም አምላክ" እንደ ሆነ፣ ትልቅ ኀይል ያለው ቢሆንም እንኳ ነገሮችን የሚሠራው እግዚአብሔር በፈቀደለት መጠን ብቻ እንደ ሆነ፣ በመጨረሻም ቀንና ሌሊት ለመሠቃየት ወደ እሳት ባሕር እንደሚጣል እናምናለን (ዘፍጥረት 3÷1-15፣ ኢሳይያስ 14÷12-17፣ ሕዝቅኤል 28÷11-19፣ ማቴዎስ 25÷41፣ ማቴዎስ 4÷1-11፣ 25÷41፣ ራእይ 12÷1-14፣ 12÷9-10፣ 20÷10)።